# የተሰማሙበት ጉዳይ ሁሉ በጎና ልክ ነው ሊባል ይችላልን?

ከፈረደ መንግስቱ

የወያኔ-ኢሃአዴግ የግፍ አገዛዝ ከሰፈነበት ጊዜ ጀምሮ ተቃዋሚ ሀይሎች በሀገርም ሆነ በውጭ ሀገር ተደራጅተው የተቃውሞ ትግላቸውን እየታገሉ ይገኛሉ። ጭቆና፤ ግፍና መከራ ያንገፈገፈው የኢትዮጵያ ሕዝብም፤ተቃዋሚ ሀይሎች በተናጠል ከሚያደረጉት ትግል ባሻገር አንድነታቸውን እንዲያጠንክሩ፤ ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ የሚል መልዕክት ሲያስተላልፍ ቆይቷል።

ይህ ጥያቄውን መሠረት በማድረግ የፖለቲካ ድርጅቶችና የኢትዮጵያ ጉዳይ ጉዳያችን ያሉ ተቋሞች የመቀናጀት፤የመተባብር እንዲሁም የመጣምር ሙከራ ሒደቶች በየጊዜው ያሳዩ ቢሆንም፤ በውጤት ደረጃ የጎላ ፋይዳ አልተገኘም። በቅርቡም በሲያትል ከተማ ከሃያ በላይ የፖለቲካ ድርጀቶች ተሰባስበው በጋራና በአንድነት ለመስራት በሚያስችላቸው አበይት ጉዳይ ላይ ሲነጋገሩ ሰንብተዋል። በመጨረሻም ለማግባባት የሚያበቁ የመንደርደሪያ ሃሳቦች ላይ ስምምነት በማደረግ የተግባር እንቅስቃሴ ውጥን እቅድ ላይ እንደደረሱ ይነገራል። እንግዲህ የዚህ ጽሁፍ የትኩረት አቅጣጫው ይህንኑ ሰብሰባን እንድ አንድ ርዕሰ ጥያቄ በማቅረብ በቂ መልስ የሚጠይቅ ይሆናል።

የሲያትሉ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ስብሰባ ሙሉ በሙሉ የተስማሙበትን ውሳኔና መግለጫ አውጥቷል። ሆኖም ባንድ ስብስባ ላይ የሚደረግ ስምምነት ሁሉ ያለቀለት፤የማያዳግም፤የመጨረሻና ፋይዳ ያለው ይሆናልን ? የሚለው ጥያቄ እጅግ የሚያወያይ ይሆናል።

እንግዲህ ይህንን ለመመለስ ከሲያትሉ ስብሰባ ምን ይጠበቅ ነበር? ከስብሰባው በፊት ምን ዐይነት ውሳኔ ላይ ሊደርስ እነደሚገባ መተነተን ይቻል ነበርን? ወይስ እንደ አዲስ የምርምር ስራውጤት ይታያልን? ይህ አጀንዳ ቀድሞ በነበሩት ኩነቶች ያልተዳሰሰ ነበረን? ወ.ዘ.ተ የነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች መነሣትና ለጥያቄዎቹም የምንሰጠው መልስ የሲያትሉን ስብስባ ውጤት ሳናሳንስ ወይም ሳንጨመረበት በትክክል እንድንገመግመው ይረዳናል።

ለሰበሰባው መጠራት ዋንኛ ምክንያት የሆነው አገራችን ካለችበት የፖለቲካ ሁኔታ አንጻር ተቃዋሚ ወይም ባለድረሻ የፖለቲካ ድርጅቶች ምን ማደረግ የጠበቅባቸዋል የሚለውን ጥያቄ መልስ ለመስጠት ነው። ስለሆነም መሰብሰባቸው አበጀ እሰየው የሚያሠኝ ነው።

ይህ ሰብሰባ በዚህ ወቅት የተጠራበት ሁኔታ መሪ ሃሣብ የሚያመለክተው የፖለቲካ ፓርቲዎች አስበውበትና መክረውበት የተፈጠረ ሳይሆን በነባራዊ ሁኔታ አስገዳጅነት ፤የመጣ መሆኑን ነው። ይህም በመሆኑ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በተናጠል የሚያደረጉት እንቅስቃሴ ከሕዝባዊ ትግል ተነጥለው እንዳይቀሩ ዕድል የሰጠ ነው ቢባል ስህተት አይመስልም። በሌላም በኩል ይህ ስብስብ ብቃትን ለመገንባት ከቻለ ደግሞ ትግሉን በመምራት ትልቅ ሚና የመጫወት እድሉ የሰፋ ይሆናል።

ከዚህ ጭብጥ ተነስተን ስብሰባውን የቃኘን እንድሆነ ይህ ሰበሰባ ግቡን መቷል ፤ልክ ነው ማለት የምንችለው፤ሕዝባችንን አስተባብሮ የሚመራው የፖለቲካ ድርጅትና ታማኝ መሪ መፈጠር ከቻለ ነው። ለዚህም ዋናው ምክንያት ሕዝባችን ይህንኑ ያልተመለሰልትን ጥያቄ አንግቦ መጓዝ ከጀመረ ረጅም ዐመታትን አስቆጥሯል። እንመራሀለን፤ ከጎንህ ነን የሚሉት ድርጅቶችና ፖለቲከኞች የህዝብን ጥያቄ ሊመልሱ ቀርቶ ትግሉ በየትኛውም መንገድ መጓዝ እንደሚገባው መረዳት ተሰኖአቸዋል። አንዴ በዘር የማንነት ፖለቲካ ሲዘፈቁ፤ ሌላ ጊዜ ሕብረ ብሔራዊነትን ሲሙኙትና ባጠቃላይ የጎላ የአንድነት ሥራ ማከናውን አቅቷአቸው እንድ ፔንዱለም ሰዐት ወዲያን ወዲህ የመወዛወዝ ባህሪ ይታይባቸዋል።

የሚገርመው ደግሞ ህዝቡን ሳያደራጁና ሳያስተባብሩ ስልጣን ፈላጊ መሆናቸው ነው። ሌላው በሲያትል ስብሰባ የታየው አስገራሚና አነጋጋሪው ጉዳይ ለህዝባችን መሪና ጀግና አመራረጣቸው ነው። እንደሚታወቀው የጀግና አመራረጥ መነሻ ገዢ ሐሳብ ሊሆን ይገባል። ይህንን በውል ሳይመረምር

ከኢሀአዴግ መንደር ላይ የሚታየውን የአንድ ወቅት ግርግር አስከፊ ሁኔታ እንደጠቋሚ ምስክር ወስዶ መሪና ጀግና የመመልመል ከሆነ እንግዲህ ህዝቡን አንጋጠህ ከገዢው መደረክ አዳኝ መልዐክህን ፈልግ እንደማለት ይመስላል። በኢሀአዴግ መንደር ውስጥ ሜዳሊያ ማደል ምን የሚሉት የፖሊቲካ ቀመር ነው።ታክቲክ ብልጠት ወይስ ክህደት? ትግሉ የፈተናቸው ያከበራቸው ህዝባዊ ጀግኖች የሉንም ማለት ነውን? ስም መጥራት እንኳን ቢያቅታቸው መላውን ሕዝብ ጀግና ማድረግ አይቻልም ነበረን? ይህ የሚያሳየው የዲያስፖራ ፖለቲከኞች ከአገር ቤቱ ትግል ጋር ምንም ዐይነት ቅርበትና ትስስር የሌላቸው መሆኑን ነው። አድርባይነትም ነው። ከኢሀዴግ መንደር ትብብርና ማበርታት ካሰፈለግ ለድርጅቶች ወይም ለጠቅላላው አባላት ጥሪ ማደረግ ሲቻል አንድን ግለሰብ ወይንም ቡድን ማንገስ አግባብ አይመሰልም።

ወቅት በሚፈጥራቸው ሁኔታዎች ላይ ተመርክዞ ያለዘላቂ ስትራታጂክ ዐላማ የሚደረግ ትንተና ሁሉ ልዩ  ልዩ ሥልታዊ ጠቀሜታ ሊያስገኝ ይችላል ተብሎ የሚታቀድ እቅድ፤ ብልጥነትና የሰላ የአዕምሮ ውጤት ሊሆን ከቶም አይችልም። እንደውም የተገላቢጦሽ ሆኖ ተጻራሪ ውጤት ሊያስከትል ይችላል።

ለህግ መንግሥታቸው እየታገሉ፤ ለክልልና ለጎሰኝነት ፖሊሲያቸው እየተከራከሩ የኢትዮጵያ ሉዐላዊትና አንድነት ዋስትና የሆነው ታሪኳ ላይ ጥቁር ነጥብ ማጠልሸት ህዝባዊ የሆነ የአንድነት አስተሳሰብ የሚያንጸባርቅ መሰረታዊ የአቋም ለውጥ ሣያደረጉ ራስን  ጀግና አድርጎ ለመሪነት ማጨት ማን ማንን አምኜ የሚያስብል አይደለምን? የሲያትል ፖለቲከኞቸ የእያንዳንዳቸው  ዐይነ ህሊና ተዐምራዊ በሆነ ሀይል በየግላቸው በትይዩ ቢቀመጡ ማን ማንን  አታለልኩ ሊል ይሆን? ማንስ ለማን ነው አድርባይ የሚሆነው? መልሱን ለህሊና ዳኝነት እንተወው።

የፖሊቲካ ፓርቲ ሚናና የሕዝብ ዐመጽ ቁርጠኝነት በሲያትሉ ስብሰባ እንዴት ታየ? በፖለቲካ ፓርቲዎች አነሳሽነት ይሁን ወይንም በሌላ የሕዝብ ብሶትና በነባራዊ ሁኔታዎች ምክንያት ህሊናዊ ሁኔታዎችን እያሟላ በመሄድ ትግሉ ወደገዘፈ አገራዊ ንቅናቄ ተለውጦ የንቅናቄውም ዐላማ በሥልጣን ላይ ያለው መንግስት ከሥልጣን ይወገድ ከሆነ እንዴት ነው መሪ ነኝ የሚል ፓርቲ(ዎች) ከስልጣን መወገድ የሚገባው? መንግሥትንስ እንዴት ነው ለድርድር የሚጠየቀው? ይህንኑ በአገራችን እየተካሄደ ያለውን የህዝብ እንቅስቃሴ ማገዝ ወይስ መቀልበስ ነው? ይህ የለውጥ እንቅስቃሴ ዐላማ ያለው፤ የከበረ መስዋዕትነት የሚከፈልበት፤ህዝብ የስልጣን ምንጭና ባለቤት መሆኑን የሚረጋገጥበት መዐበል እንጂ በአውጫጭኝ  ወይንም በሸንጎ ምክክር በሚደረስ ስምምነት ብቻ የሚሠራ አይደለም።

አሁን ያለው ትግል በህዝቡና በኢህአዴግ መሀል ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ትግሉን በሚገፋው ህዝባዊ መዐበልና የማዕበሉን አቅጣጫ በመዘወር ወደሌላ አቅጣጫ ሊመሩት በሚሹ የድል አጥቢያ ሥልጣን ፈላጊዎች ጋር ጭምር ነው። ልብ በሉ ብሔራዊ መገባባትና እርቅ ከገዢው ፓርቲ ጋር አያስፈልግም ለማለት ፍጹም አይቃጣም። ባልተነጋገሩበት ሐሣብ ላይ ልተች የሚል ቢኖር የዐዕምሮው ሁኔታ የሚያጠያይቅ ይሆናል። ከቶም ሊሆን አይገባም። ይዚህ ታላቅ ተግባር ባለቤት ዛሬ በደረስንበት የዕድገት ደርጃ ማን ሊሆን ይገባል የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል። ይህውም የተቃዋሚ ድርጅት ወይንስ እንቢ አሻፈረኝ ያለው ህዝባችን ወይንስ ማን? ሕዝቡ ከብዙ ትዕግስትና በደል በኋላ በመሰዋዕትነት ገዢውን መንግሥት በማስጨነቅ ላይ እያለ፤ መሪ የፖለቲካ ድርጀቶች መጠየቅ ያለባቸው ዕርቅን ሳይሆን ሕዝባዊ ሥልጣን ወደ ህዝቡ እንዲመለስ ማድረግን ነው። የብሔራዊ ዕርቅና መግባባት በሶስተኛ አካል ወይም በሌሎች ተቋሞች አማካይነት ሊጠይቅ ይችላል ወይም በመንግስት ሊጠራ ይገባል። ተቃዋሚ ድርጀቶች ግን ተደራዳሪ ሆነው ከህዝቡ ጎን መቆም እንጂ ትግሉን የሚቀለብስ ከወያኔ እጅ ችሮታን የሚጠየቅ የእነሱ ሀሳብ መሆን አልነበረበትም ። የሲያትሉ ውሣኔ ከፓሪስ "2" እና ሌሎች ልዩ ልዩ የሆኑ አንድነትን ለመፍጠር ከተደረጉ የተቃዋሚ ሃይሎች ስብሰባ ሙከራዎች በምን ይለያሉ? ዛሬም አልመሸም። ከስህተት መማር ብልህነት ነው።

ከሲያትሉ ስብሰባ ይጠበቅ የነበረው

- ወያኔ-ኢሃአዴግ ከሥልጣን መነሳት እንዳለበት ሙሉ በሙሉ መስማማት!
- የአመራር ሃላፊነቱን ህዝብ በነጻ ውድድር ለሚመረጥ የፖሊቲካ አካል መሰጠት እንዳለበት፤
- የሚቋቋመው ህዝባዊ መንግሥት ሥልጣኑን እስከሚይዝ ድረስ የመንግስት ስልጣን ክፍተት እንዳይፈጠር በምትኩ የባለ አደራ ወይም ሌሎች አማራጮች በመጠቀም መንግስት መቋቋም እንዳለበት ፤
- ኢህአዴግ ስምምነት ለተደረሰበት አማራጭ ተተኪ ወይንም ለባለአደራው መንግስት ሥልጣኑን ማስረከብ አለበት!! የሚል ግልጽ አቋም ይዞ መውጣት ይጠበቅበት ነበር። እነዚህንም ውሳኔዎች ድጋፍ የሚያገኙበትና ለአፍጻጽም የሚያመቹ መዋቅራዊ ተቋማትንና የእነዚህንም ተቋማት የሰራ ውጤት እይገመገመ የሚያተጋ አካል የሚፈጠርበትን መንገድ ማመቻቸት ነበር።
- የባለአደራ መንግሥት እንዴት መምጣት ይቻላል የሚለውን ዝርዝር እቅድና ንድፈ ሐሣብ መነደፍ ይግባው ነበር።

ከእንግዲህ በአገር ቤትም ሆነ በውጭ ያለ ኢትዮጵያዊ የሚታገለው ለዚህ ብቻ መሆን ነበረበት ሆኖም ግን የሲያትሉ ስብሰባ ከ ፓሪስ "2" እና በተለያዩ ወቅቶች ከተሞከሩት ሁሉ ባልተሻለ ሁኔታ ከወያኔ መንደር ድርድርን የጠየቀ ይመስላል። እንደ "ግዮን ኮንፈረንስ" ወደ አገር ቤት በመሔድ ከወያኔ ጋር የጋራ ምክር ለመምከር የሚል ሐሣብም ተቃፕቷል። ይህ አቋም ምን ያህል የህዝቡን ትግል የኋሊት የሚጎትት፤ በማር የተለወሰ መርዝ አይደለምን? ለዚህ ነበር የሲያትሉ ፖለቲከኞች "ፕጃዬን አየሁት ልኳንዳ ቤት ተንጠልጥሎ" እንዲሉ ህዝባችን ጭቆና በቃኝ ብሎ እያከናወነ ያለውን ሕዝባዊ ዐመጽ ወደ ጎን ለመግታት የሞከሩት። ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ ያለበለዚያ ድንጋይ ነው ብለው ይጥሉሃል የሚባለውን ብሂል ማስተዋል ጭራ ሆኖ ከመቁጠር ያድናልና ምከሩበት።
የወሰደውን ያህል ጊዜ ይፍጅ እንጂ አድርባዮችና የኢትዮጵያ ጠላቶች ከህዝብ ትከሻ ላይ መራገፋቸው አይቀርም። ህዝቡም የሥልጣን ባለቤት ይሆናል። የታሪክም ፍርድ በአደባባይ ይነገራል። የቱንም ያህል አስመሳዮች ቢያላዝኑም፤ እውነትና ንጋት እያደር የገለጣል እንዲሉ ዕውነት በነሱም ላይ ቢሆን ስለራሷ ለመመስከር ብቃት እንዳላት አትጠራጠሩ።
ብሄረተኛውና፤ የአንድነት ሃይል ነን ባዩም በዐንድነት ተሰባስበው ሕገ መንግስቱንና የክልል አወቃቀሩን በመደገፍ ተስማማን ስለተባባሉ የአንድነት ኀይሉን መሸነፍ አያሳይም፤ እንደውም ብኄረተኛ የሚመራው ስለሚመስል ላንድነት ኀይሉ የጥንካሬ ምንጭ ይሆናል።
ስምምነት ሁሉ ልክ ከተባለ ሣጥናዔልም ከመሰሎቹ ጋር ሆኖ ያደረገው የጋራ ስምምነትና ውሳኔ ትውልድ በጎ ነው ብሎ በተቀበለ ነበር። ነገር ግን ሀሰትን ለተቀበለ እውሸትን ከፍ ከፍ ላደረገ ሁሉ እውሸት እንደተራራ ቢከመር አንዲት ቅንጣት እውነት አይሆንም።

# ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር